**Ethiopian National Transitional Council**
P.O.Box 40963
Arlington, VA 22204
Tel: 1-703-659-6000 (US and Canada)
Tel: +44-7958-487-420 (Europe, Mid. East and Africa)
Email: contact@etntc.org
Website: www.etntc.org

August 22, 2014

# የበርማ የስደት መንግስት ለነጻነት ትግል አስኳል በመሆን የመራው የትግል ተሞክሮ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት ጁላይ 27 2014 ባወጣው መግለጫ፤ የወያኔን አፓርታይድ ስርዓት ለማስወገድና በሀሉ አቀፍ ህዝባዊ የሽግግር መንግስት ለመተካት ጥንስስ በመሆን መሰረት የሚጥልና የተበታተነውን ትግል በአንድነት ሊመራ የሚችል የአንድነት ሀይል (የስደት መንግስት እንደአማራጭ) እንዲቋቋም ሀገራዊ ጥሪ ማቅረቡ የሚታወስ ነው (ለማንበብ እዚህ ላይ ይጫኑ http://goo.gl/KYP32s) ። ምክር ቤቱ ጥሪውን ተከትሎ ከሚመለከታቸው አካላትና ድርጅቶች ጋር የሁለትዮሽ ውይይት በማካሄድ ላይ ይገኛል። እስካሁን የተደረጉ ውይይቶች በአብዛኛው አበረታቶች ሲሆኑ አንዳንድ ወገኖች ደግሞ ምንም አይነት የተለየ አማራጭ ሳያቀርቡና የሌሎች አገራትን ተሞክሮ በጥልቅ ሳይፈትሹ አግዝፈው በመመልከት አስቸጋሪና ሊተገበር የማይችል አድርገው ያምናሉ። የኢትዮጲያ ሕዝብ በሰቆቃ ውስጥ ሆኖ ፍዳውን በሚያይበትና ሀገራችን በመንታ መንገድ ላይ በምትገኝበት በዚህ ወሳኝ ወቅት እለታዊ ችግሮችን ከመተንተን ባለፈ የአማራጭ መፍትሔ በማቅረብና ስምምነት ላይ በመድረስ በአንድነት ትግሉን መምራትና ማካሄድ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆኗል።

የአንድነት ሀይል (የስደት መንግስት እንደአማራጭ) የማቋቋም አስፈላጊነትን አስመልክቶ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ የነበሩና በጨቋኝና አምባገነናዊ ስርዓቶች ተገፍተው ከአገር ውጭ የስደት መንግስት በማቋቋም ከታገሉና በትግል ላይ ካሉ የሌሎች ሀገራት ህዝቦች የትግል ሂደት በመመርመር ከተሞክሮው ግንዛቤ መውሰድ ለምናደርገው ትግል በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይም ምርጫ 97ን ተከትሎ ወያኔ እያካሄደ ካለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ አፈና፤ እስር፤ ግድያ፤ በዘር ከፋፍሎ ማጋጨትና ዘረፋ ጋር በከፊልም ቢሆን ተመሳሳይ ታሪክ ያላት በርማ የምትባለውን አገር በምሳሌነት መውሰድ ጠቃሚ ነው።

በርማ በደቡብ ምስራቅ እስያ የምትገኝ በታይላንድና ባንግላዴሽ የምትዋሰን ሀገር ናት። በሲ.አይ ኤ የመረጃ ሰነድ መሰረት የበርማ የቆዳ ስፋት 670ሺህ ካሬ ኪ/ሜትር ይገመታል። ይህ ማለት የኢትዮጵያ ግማሽ ያህል ስፋት አላት ማለት ነው። የህዝቧ ብዛትም ወደ 56 ሚሊዮን ይገመታል። በርማ በጃፓን ቅኝ አገዛዝ ስር የነበረች ሲሆን በ1948 ዓ.ም እ.ኤ.አ በእንግሊዝ እርዳታ ነጻነቷን አግኝታለች።

በ1962 ዓ.ም እ.ኤ.አ ጄኔራል ነ ዊን የተሰኙ የሰራዊቱ አዛዥ በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን ተቆጣጥረው በሀገሪቱ ላይ የወታደራዊ ጁንታ ይመሰርታሉ። ህዝቡንና ሀገሪቱን በፍጹም የጭቆና ቀንበር ውስጥ በማስገባታቸው በአለም ደረጃ በሰብአዊ መብት ረገጣ በቀደምትነት ከተመዘገቡት ሀገራት ውስጥ በርማ ለመገኘት በቃች። ጁንታው የዲሞክራሲ ሀይሎችን ሙሉ ለሙሉ ከሀገሪቷ አጥፍቶ የበርማ ሶሻሊስት ፕሮግራም ተብሎ የሚጠራው የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አስተዳደርን አሰፈነ።

ሀገሪቷ ከጎርቤት ሀገራትና ከሌሎች የአለም ሀገራት የተገለለች ብቸኛ እንድትሆን በማድረጉ በአለም ድሀ ከሚባሉት ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በመንግስት ባለስልጣናት የሚደረገው ዘረፋና የአስተዳደር ብልሹነት በሩዝ ምርት አቅራቢነት ትጠቀስ የነበርችውን የበርማን ኢኮኖሚ አሽመድምዶ ህዝቡን የድህነት ማቅ አለበሰው። የህዝቡ ችግር ከሚሸከመው በላይ በመድረሱ በ1987 ዓ.ም እ.ኤ.አ የበርማ ህዝብ መሪዎቹን በመቃወም በሕዛባዊ እምቢተኝነት ወደ አደባባይ ተመመ።

በህዝብ የተቀሰቀሰው አብዮት ምንም እንኳን ለብዙ ሺህ በርማውያን ህይወት መጥፋት ምክንያት ቢሆንም አመጹ እያየለ መጥቶ በ1988 ዓ.ም ፈላጭ ቆራጩ የወታደራዊ ጁንታ ጄኔራል ዊን ከስልጣን ለቀቁ። በህዝባዊ ማእበልና በዘር ፖለቲካ የተናጠችውን ሀገር በማረጋጋት ሰበብ የወታደሩ ክፍል ስልጣኑን ሳይለቅ፤ የመድበለ ፓርቲ ዲሞክራሲ በመፍቀድ ነጻና ህዝባዊ ምርጫ ለማደረግ ቃል በመግባትና በማዘናጋት አመጹን በተወሰነ መልኩ ለጊዜው አረጋጋው።

በዚህ መሰረት መሰረት በ1990 ዓ.ም እ.ኤ.አ በበርማ ታሪክ የመጀመርያውን ነጻ ምርጫ ለመካሄድ በቃ። በአጭር ጊዜ ተደራጅተው የወታደራዊውን ገዥ ፓርቲ በምርጫ ከገጠሙት በርካታ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ አንዱ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ሊግ (National League for Democracy) በመባል የሚታወቀው በከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ በምርጫ አሸናፊ መሆኑ ተረጋገጠ።

በሃገራችን ምርጫ 97ን ተከትሎ ወያኔ እንዳካሄደው ድርጊት፤ የበርማም ወታደራዊ ጁንታም በግፍ የመግዛት ጥም ገና ያልወጣለት የአምባገነኖች ስብስብ በመሆኑ ውጤቱን በጸጋ ሊቀበለው ፈቃደኛ አልሆነም። የህዝብ ድምጽ መነጠቁን ተከትሎ በተነሳው ህዝባዊ ቁጣ ብዙ የበርማ ዜጎች ህይወት በጨካኙ አምባገነናዊ አገዛዝ የጥይት እራት ሆኑ። ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የተቃዋሚ ድርጅት አመራሮች እየታደኑ ወደ ወህኒ እንዲወርዱ ተደረገ። ገሚሱም ወደየጎርቤት ሀገራት ተሰደደ። የአሸናፊው ፓርቲ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ሊግ (National League for Democracy - NLD) መሪና የኖቤል ተሸላሚ የሆኑት ወ/ሮ አን ሳን ሱቺ ከሰው ጋር እንዳይገናኙና በቁም እስር እንዲቆዩ ተደረገ።

ይህንን አይን ያወጣ የህዝብ ድምጽ ንጥቂያ አንቀበልም በማለት ከእስርና ጭፍጨፋው ማእበል ተርፈው ወደ ጎረቤት ሀገር የተሰደዱት የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች በበርማና በታይላንድ የድንበር ከተማ ላይ National Coalition Government Union of Burma (NCGUB) በሚል ስም በስደት የሚንቀሳቀስ መንግስት አቋቋሙ። የተቋቋመው ይህ የስደት መንግስት የአን ሳን ሱቺን NLD ፓርቲ ጨምሮ በርካታ ተቃዋሚ ሀይሎችን ያቀፈ ነበር።

ይህ የበርማ የስደት መንግስት መቀመጫውን በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ በማድረግና ለበርማ የነጻነት ትግል አስኳል በመሆን በተከታዮቹ አመታት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን መርቷል። የስደት መንግስቱ የተቃዋሚዎችን ድምጽና ትግል አንድ አድርጎ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግሉን ሲመራና ሲያስተባብር ቆይቷል። በአለም መንግስታትም ከበሬታን እያገኘ በመሄዱ፤ የተለያዩ ሀገር ባለስልጣናትን በማነጋገርና ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራዎችን በመስራት በበርማው ጨቋኝ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ለማስደረግ ችሏል።

በዶ/ር ሴይን ዊን የሚመራው የበርማ የስደት መንግስት በተለያየ ጊዜ ከአሜሪካና ከአውሮፓ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ተወካዮች ጋር ውይይት በማድረግ በሀገሪቱ ጉዳይ ላይ ተጨባጭ የሆኑ ስራዎችን ሰርቷል። በበርማ የነጻነት ትግል ውስጥ በዲፕሎማሲ በኩል ካደረጋቸው አስተዋፅኦዎች ውስጥ፤

በ 1997 ዓ.ም እ ኤኤ የአሜሪካው የህግ መወሰኛ ምክር ቤት የኮሄን-ፋይንስታይን ማሻሻያ *Cohen-Fienstein Amendment-Section 569 of the Foreign Operations and Appropriations* Act በበርማ መንግስትና በባለስልጣናቱ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚና የመንቀሳቀስ መብትን የሚገድብ እቀባ ህግ እንዲፀድቅ ትግል አድርጓል።

ለተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት የበርማን ፖለቲካ ቀውስ ሳይታክት በማስገንዘብ፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የበርማን ህዝብ ሰብአዊ መብትና ነጻነት መከበር የሚጠይቁ ውሳኔዎችን (resolutions) እንዲያፀድቅ ከፍተኛ ትግል አድርጓል። *UN RESOLUTIONS A/RES/47/144, A/RES/48/150, A/RES/49/197*,etc

የስደት መንግስቱ ከውጭ ትግሉን ሲያካሂድና ግፊቱን ሲያደርግ ከውስጥም ከውጭም ያለው ግፊት በመጠንከሩ በ2010 ዓ.ም የወታደራዊው መንግስት በድጋሚ ህዝባዊ ምርጫ ለማካሄድ ተገደደ። በተለመደው የአምባገነኖች ታክቲክ በምርጫው የተቃዋሚ ሀይሎች ተመጣጣኝ የመጫወቻ ሜዳ ካለማግኘታቸውም በላይ ምርጫው ግልጽና ፍትሐዊ ያልነበረ በመሆኑ ብዙዎቹ ድርጅቶች እራሳቸውን ያገለሉ አለበለዚያም ለይስሙላ የተወዳደሩ ነበሩ።

ምንም እንኳን ገዥው ፓርቲ ምርጫውን በመንጠቅ በጉልበት አሸናፊነቱን ቢያውጅም የትግሉን አቅጣጫ ሊያስቀይረው ባለመቻሉ የተቃዋሚ ሀይሎች በአንጻራዊ ነጻነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ ሁኔታዎች እንዲመቻቹላቸው ተደረገ። የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላት አን ሳን ሱቺን ጨምሮ ከሞላ ጎደል በነጻነት በመንቀሳቀስ በ 2012 ዓ.ም ምርጫ በሀገሪቱ ከሚገኙት ከተሞች በዋና ዋናዎቹ ላይ ተወዳድረው በአሸናፊነት ወደ ፓርላማ ገብተዋል። ሌሎች የተቃዋሚ ድርጅት አመራሮችም በአሁኑ ሰአት ወደ አገራቸው ተመልሰው በመታገል ላይ ይገኛሉ።

ሀገሪቱ ውስጥ እይታየ ያለውን የፖለቲካ ለውጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ ለነጻነት ሲንቀሳቀስ የነበረው የስደት መንግስት በ September 2012 ዓ.ም እራሱን ማክሰሙን (dissolve) አስታውቋል። አባል ድርጅቶቹም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በፖለቲካው ለመሳተፍ የበኩላቸውን እያደረጉ ነው። ምንም እንኳን የሀገርቱ ችግር ገና ብዙ የሚቀረው ቢሆንም በተሻለ ጉዞ ላይ ትገኛለች።

አገራችን ኢትዮጵያ በወያኔ ያፓረታይድ  ስርዓት ስር እየማቀቀች በምትገኝበት በዚህ ወሳኝ ወቅት። ተቃዋሚ ሀይሎች በየፊናችን የምናደርገው ሩጫ ወደለውጥ መንገድ ሊመራን ካለመቻሉም አልፎ፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ግራ በማጋባትና ተስፋ በማስቆረጥ ለጨቋኙ የወያኔ መንግስት የተመቸ ሁኔታ ፈጥሮለታል። ለዘመናት ተመሳሳይ ነገሮችን በማድረግ የተለየ ውጤት ከመጠበቅ አባዜ በመውጣት ለየት ያሉ አማራጮችን መቀበል ወይም ማቅረብ አራሱን የቻለ የፖለቲካ ጥበብ መሆኑን በመገንዘብና ልዩነታችንን በማጥበብ ከላይ ባጭሩ ለምሳሌነት የቀረበውን የበርማ ህዝብ የትግል ታሪክና የሌሎችንም ተሞክሮ በምሳሌነት በመውሰድ ኢትዮጲያዊነትን መሰረት ያደረገ አንድ ወጥ አመራር ያለው የተባበረ ሀይል (የስደት መንግስት እንደ አማራጭ)  በማቋቋም ስርአቱን ማስወገድ ወይም ማስገደድ የወቀቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው።

ትግሉንና ድሉን የጋራ እምናደርገው፤ ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል ያንድነትና የአማራጭ ሃይል ነጥሮ ሲወጣ በመሆኑ ዛሬም እንደወትሮው ለሀገር ወዳድና ነጻነት ናፋቂ ወገኖችኖች፤ እንዲሁም ለመገናኛ ብዙሃን ተቋማት በዚህ ዙሪያ አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጉ ሃገራዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በተመሳሳይ የተለያዩ ድርጅቶች አሉኝ የሚሏቸዉን የአማራጭ መፍትሄዎችን ለህዝብ ለውይይት ይፋ እንዲያደርጉ እንጋብዛለን።

የኢትዮጵያ በሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት በመርህ ደረጃ የወያኔ/ኢሕአደግ ስርአትን ማስወገድ መተካት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች እንደሁኑ በጽኑ ያምናል። ይህንን ጭብጥ በተመለከተ ለመቋጫ ይረዳ ዘንድ  በሃገር ውስጥ ከሚገኙ የፖለቲካ ድረጅት መሪዎች ከተናገሩት ለናሙና ይህንን በመጫን ያድምጡ http://goo.gl/S2g7Ep

**ትግሉንና ድሉን የጋራ እናድርገው!**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ምክር ቤት